# የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

# የማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ፣ ግዥ፣ አቅርቦትና ስርጭት

## መመሪያ **459/2013**

መስከረም 2011 ዓ/ም

አዲስ አበባ

መግቢያ 3

ክፍል አንድ 4

ጠቅላላ 4

1. አውጭው ባለስልጣን 4

2. አጭር ርዕስ 4

3. ትርጓሜ 4

4. የተፈጻሚነት ወሰን 5

6. የመመሪያው ዓላማ 5

7. የመመሪያው አስፈላጊነት 6

ክፍል ሁለት 6

የማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ 6

ክፍል ሦስት 7

የማዳበሪያ ግዥ ሂደት 7

15. የፋይናንስ አቅርቦት 7

16. የማዳበሪያ ግዥ አፈጻጸም 7

ክፍል አራ 10

የማዳበሪያ አቅረቦት፣ የዋጋ አወሳሰን እና ስርጭት 10

17. የማዳበሪያ አቅርቦት 10

18. የማዳበሪያ ዋጋ አወሳሰን 10

19. የማዳበሪያ ስርጭት 10

ክፍል አምስት 11

የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት 11

20. የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር 11

21. የማዳበሪያው አስመጭ ድርጅት ተግባርና ሀላፊነት 12

22. የክልል ግብርና ቢሮዎች እና ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች 13

23. የትራንስፖርት ሚኒስቴር 15

24. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት 16

ክፍል ስድስት 17

ስለ ቅሬታ አቀራረብ 17

ክፍል ሰባት 18

ስለ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 18

29. የተሻረ መመሪያ 18

30. መመሪያውን ማሻሻልና መተግበር 19

31. መመሪያው የሚፈፀምበት ጊዜ 19

መግቢያ

እያደገ የመጣውን የአርሶ አደሩን የማዳበሪያ ፍላጎት ለማሟላት ማዳበሪያ በየአመቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ ተገዝቶ እየገባ ሲሆን በአገር ውስጥ የማሰራጨት ስራም ከፍተኛ ገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ የማከማቻ አቅምና ልምድ የሚጠይቅ ነው፡፡ የፍላጎት ዳሰሳ ችግር፣ የዓለም የማዳበሪያ መግዣ ዋጋ መናር ፣ የአገር ውስጥ ማጓጓዣና የሌሎች ወጭዎች ጭማሪ በማሳየታቸው ለአርሶ አደሩ በችርቻሮ የሚሸጥበት ዋጋ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

ይህ አዝማሚያ በዓለም የምርቶች ዋጋ መለዋወጥ ምክንያት እየቀጠለ የሚሄድ ከሆነ የአርሶ አደሮችን አቅም በመፈታተን በማዳበሪያ አጠቃቀም ብሎም በምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያስከተለ ነው፡፡

አርሶ አደሩ ማዳበሪያን በወቅቱ፣ በሚፈልገው ጥራት፤መጠንና በተወዳዳሪ ዋጋ አግኝቶና ተጠቅሞ ምርታማነቱን ለማሳደግ እንዲችል የአቅርቦት ስርዓቱን የሚያቀላጥፍና ወጭን የሚቆጥብ የአሰራር መመሪያ መቀየስና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ከማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ ጀምሮ ተጠቃሚው አርሶ አደሩ ዘንድ እስከሚደርስ ድረስ የሚኖሩ የአቅርቦት እንቅስቃሴዎችንና ተግባራትን ከግምት በማስገባት እንዲሁም ዘመናዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል ይህ የማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ፣ ግዥ፣ አቅርቦትና ስርጭት መመሪያ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ/ም አንቀጽ 09 ንዑስ አንቀጽ ረ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አውጭው ባለስልጣን

የግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከግብርናና እንስሳት ግብአቶች አቅርቦትና አገልግሎት ጋር ተያይዝው በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር 137/91 እና ስለ ማዳበሪያ የወጣ አዋጅ ቁጥር ----- በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ፣ ግዥ፣ አቅርቦትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 439/ 2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. ትርጓሜ

በማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር 137/91 እና ስለ ማዳበሪያ የወጣ አዋጅ ቁጥር ----- እንዲሁም በህበረት ስራ አዋጅ ቁጥር 147/91 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሀረግ በድጋሚ ትርጉም መስጠት ሳያስፈልግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ሆኖ፤

3.1. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ማለት ነው

3.2. "ሚኒስትር ዴኤታ ማለት" የግብርና ግብዓት እና ምርት ግብይት ሚኒስትር ዴኤታ ማለት ነው

3.3. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3.4. "ማዳበሪያ ማለት" በተፈጥሮ የተገኙ ወይም በፋብሪካ የተቀነባበሩ ቁሶችን ማለት ሲሆን፤ ለተክሎች እድገት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ለማሟላት በአፈር ውስጥ ወይም በተክሎች ላይ የሚጨመር ነው፣

3.5. "የፍላጎት ዳሰሳ " ማለት የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በየደረጃው በዓይነት በመጠን እና በሚያስፈልግበት ቦታ ለይቶ ማቅረብ ማለት ነው፣

3.6. "ግዥ" ማለት ማዳበሪያን ከአምራች ወይም ከአቅራቢ ገዝቶ ማቅረብ ማለት ነው፣

3.7. "አቅርቦት" ማለት ከአምራች ወይም ከአቅራቢ በመግዛት በማእከላዊ መጋዘን ለተረካቢ የሚቀርብ ማለት ነው፣

3.8. "ስርጭት" ማለት ማዳበሪያን ለተጠቃሚዎች ማድረስ ማለት ነው

3.9. "አጓጓዥ ማለት" ድንበር ተሻጋሪ፣ ወይንም በአገር ውስጥ ብትን ጭነትን ለማጓጓዝ ፍቃድ ያገኘ የግል ትራንስፖርተር ወይም ማህበር ማለት ነው፣

3.10. "አስመጪ" ማለት ማዳበሪያን ለማስመጣት እና ለአገር ውስጥ ማስረከቢያ ማዕከላት እንዲያስረክብ አግባብ ባለው አካል ስልታን የተሰጠው ማለት ነው፡

3.11. "ማዕከላት" ማለት ማዳበሪያ ከወደብ በቀጥታ ማዳበሪያ የሚራገፍበት ቦታ ማለት ነዉ፣

3.12. "የማስረከቢያ ዋጋ ማለት" አስመጪው ከወደብ ማዳበሪያን ለማዕከላት የሚያስረክብበት ማለት ነው

3.13. "ምጥን ማዳበሪያ" ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የማዳበሪያ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ሲሆን በሚመረትበት ጊዜ ምንም ዓይነት ኬሚካላዊ አፀግብሮት የማይኖረው ነው፣

3.14. "የኢትዮጵያደረጃ" ማለት በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ የወጣ የማዳበሪያ ደረጃ ማለት ነው፤

3.15. "የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት" ማለት የማዳበሪያ ጥራት በኢትዮጵያ ደረጃ መሰረት ያሟላ መሆኑን ምዘና የሚያካሂድ ድርጅት ነው፡፡

3.16. "የኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት ሰዎች በፍቃድኝነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻቸዉን በጋራለመፍታት ሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድየሚያስተዳድሩት ማኅበር ነዉ፡፡

3.17. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፤ ውኃ የሚሟሟና በፈሳሽ መልክ ወይም በርጭት ጥቅም ላይ የሚውል ማዳበሪያ ነው፤

4. የተፈጻሚነት ወሰን

4.1. በአዋጅ ቁጥር -------- የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ክልላዊ መንግስታትና የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ በሚገኙ በማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ፣ ግዥ፣ አቅርቦ እና ስርጭት ስራ ላይ በሚሳተፉ አካላት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6. የመመሪያው ዓላማ

6.1. የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በሚፈለገው ጥራት፣ መጠን በተመጣጣኝ ዋጋ እና በወቅቱ ለማቅረብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ነው፡፡

7. የመመሪያው አስፈላጊነት

7.1. አርሶ አደሩ ማዳበሪያን በወቅቱ፣ በሚፈልገው ጥራት፤መጠንና በተወዳዳሪ ዋጋ አግኝቶና ተጠቅሞ ምርታማነቱን ለማሳደግ እንዲቻል ማዳበሪያ ስለሚሰራጭበት ሁኔታ፣ የስርጭት አውታርን በማስፋፋት ቀልጣፋ፣ ወጭ ቆታቢ፣ ሁሉ አቀፍ እና ወቅታዊ የማዳበሪያ ስርጭት መቀየስና ተግባራዊ የሚያስችል አሰራር በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተዋናኝ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳይ ዝርዝር የማዳበሪያ ፍላጎት፣ ግዥ ፣ አቅርቦት እና ስርጭት የአሰራር መመሪያ የማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፣

7.2. በመጠን እና በአይነት እያደገ የመጣውን የአነስተኛ አርሶ አደሮችና የሰፋፊ እርሻ ባለቤቶች የማዳበሪያ ፍላጎት በወቅቱ፤ በጥራትና በቅልጥፍና እንድሁም በሁሉም የምርት ወቅቶች ማሟላት እንዲቻል፣ አስተማመኝ የሎጂስቲክስ አቀረቦት እና የፋይናንስ አቅርቦት፤ አማራጭ እና ውጤታማ የሆነ የግዥ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

## ክፍል ሁለት

## የማዳበሪያ ፍላጎት ዳሰሳ

8. የቀበሌ የማዳበሪያ ፍላጎት በልማት ጣቢያ ሰራተኞች አማካይነት እያንዳንዱን አርሶ አደር በማማከር እና ከእርሻ መሬቱ ጋር በማገናዘብ በወቅቱ ጥቅም ላይ የሚውለውን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ለመስኖ፣ለበልግና ለመኸር በመለየት በጣቢያ ያለውን መጠን በግምት ውስጥ በማስገባት ይታቀዳል፡፡ ይህም በቀበሌ ደረጃ በግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ውይይት በማድረግ በቀበሌ አስተዳደሪ ጸድቆ እስከ ግንቦት 15 ለወረዳ ግብርና ይላካል፣

9. በመስኖ፣ በበልግና በመኸር ተለይቶ የቀረበው የቀበሌው የማዳበሪያ ፍላጎት ከወረዳው የልማት አቅጣጫ አንጻር በግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ውይይት በማድረግ በወረዳ  አስተዳዳር ጸድቆ እስከ ግንቦት 30 ድረስ ለዞን እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ይቀርባል፡፡

10. ከወረዳ የቀረበው ዕቅድ በዞን ደረጃ ባለው አስተባባሪ ኮሚቴ ውይይት ተደርጎበት በዞኑ ውስጥ ያለው የግብርና ግብኣትና አገልግሎት ማዕከላትን ታሳቢ በማድረግ አጽድቆ እስከ ሰኔ 10 ድረስ ለክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ይቀርባል፣

11. ከዞኑ የቀረበው ዕቅድ ክልል ደረጃ ባለው የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ውይይት ተደርጎበት በክልል ፀድቆ እስከ ሰኔ 20 ድረስ ለፌዴራል ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ለግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት ዘርፍ ይቀርባል፣

12. የማዳበሪያ አስመጪዎች በሁሉም ክልሎች ያሉትን የግልና የመንግስት እርሻዎች ፍላጎት በማሰባሰብ ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ያቀርባል፣
13. ከክልሎች እና ከሌሎች አቅራቢዎች በቀረበው ፍላጎት መሠረት በፌዴራል የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ ካለው ሀገራዊ የልማት ግብ ጋር በማገናዘብ ለውሳኔ ለግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት ዘርፍ እስከ ሀምሌ 15 ያቀርባል፣
14. በፌዴራል የግብዓት አስተባባሪ ኮሚቴ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በማድረግ የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፀድቆ የግዥ ትዕዛዝ እስከ ሀምሌ 30 ድረስ ለአስመጪው ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማዳበሪያ ግዥ ሂደት

15. የፋይናንስ አቅርቦት
    15.1. የክልል ግብርናና እንስሳት ሀብት ቢሮ /የክልል ህብረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ/ በኩል በክልሉ ዓመታዊ የግብዓት ፍላጎት መሠረት የአፈር ማዳበሪያ መግዣ የፋይናንስ ፍላጎት በመለየት እስከ ሀምሌ 30 ድረስ ይቀርባል፣
    15.2. የፌዴራል ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር የግብርናና ግብዓትና ምርት ግብይት ዘርፍ የሀገሪቱን የግብዓት መግዣ የፋይናንስ ፍላጎት በተለይም የአፈር ማዳበሪያን በመለየት እስከ ነሐሴ 15 ድረስ ለብሄራዊ ባንክ ያቀርባል፣
    15.3. ከብሄራዊ ባንክ የተፈቀደውን እና የክልሎች የግዥ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ለክልሎች የተፈቀደው የገንዘብ መጠን በግብዓት ዓይነት ተለይቶ እንዲያውቁ ይደረጋል፣

16. የማዳበሪያ ግዥ አፈጻጸም
    16.1. አስመጪው ከግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር በቀረበው ዝርዝር መግለጫ መስፈርት(specification)መሠረት ዓለም አቀፍ ጨረታ ያወጣል፣ከግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ሲፈቀድ ሌሎች አማራጭ የግዥ ዘዴዎችን ይጠቀማል፣
    16.2. አስመጪው የማዳበሪያ ግዥ የጨረታ ኮሚቴ አማካይነት የቀረበውን ሰነድ በመስፈርቱ መሠረት የቴክኒክና የፋይናንስ ግምገማ በማድረግ እና በማወዳደር አጣርቶ ውጤቱን ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ያቀርባል፣
    16.3. ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስትርም በመስፈርቱ መሠረት የቴክኒክ ሥራውን የቴክኒክ ኮሚቴ አጣርቶ ለፋይናንስ ኮሚቴ ያቀርባል፣

16.4. የፋይናንስ ሥራውን በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የግብርና ግብዓትና ገጠር ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ከአስመጪዎች ትክክለኛነቱን በማረጋገጥና ከቴክኒክ ኮሚቴ የቴክኒክ ግምገማ ሪፖርት በመቀበል ለብሄራዊ የማዳበሪያ ግዥ አብይ ኮሚቴ ያቀርባል፣

16.5. ብሄራዊ የማዳበሪያ ግዥ አብይ ኮሚቴ የግምገማ ውጤቱን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ግዥ እንዲፈጸም የውሳኔ ሀሳብ ለዘርፉ ሚኒስትር ዴኤታ ያቀርባል፤

16.6. ሚኒስትር ዴኤታውም የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መሰረት በማድረግ አጽድቆ ግዥ እንዲፈጸም ለአስመጪው በ3 ቀናት ውስጥ ያሳውቃል፣

16.7. አስመጪውም የጸደቀውን የግዥ ውሳኔ መሠረት ለአሸናፊ አቅራቢዎች በ3 ቀናት ውስጥ የውሳኔውን ሀሳብ ያሳውቃል፡፡

16.8. የማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ ስለማቋቋም

የማዳበሪያ ግዢ ኮሚቴው አንድ አብይ እና የቴክኒክ ኮሚቴ ይኖሩታል፣

16.8.1. የማዳበሪያ ግዥ አብይ ኮሚቴ

16.8.2. የማዳበሪያ ግዥ አብይ ኮሚቴ አባላት

ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የተውጣጣ አባላት ይኖሩታል፣

| | | |
|---|---|---|
| 1. | በግ.እ.ሀ.ሚ/ር የግብርና ግብዓቶች ግብይት እና ገጠር ፋይናንስ | ሰብሳቢ |
| 2. | በግ.ግ.ግ.ገ.ፋ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ | አባልና ፀሀፊ |
| 3. | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር | አባል |
| 4. | የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር | አባል |
| 5. | የፌደራል ህብረት ስራ ኤጀንሲ | አባል |
| 6. | የማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን | አባል |
| 7. | የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ | አባል |
| 8. | የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ | አባል |
| 9. | የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና | አባል |

16.8.3. የአብይ ኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነት፤

16.8.3.1. አማራጭ የማዳበሪያ ማስገቢያ ወደቦችን በማጥናት የማዳበሪያ ግዥዉ በግዜ ሰሌዳው መሰረት እንዲገዛ ሀሳብ ያቀርባል፣

16.8.3.2. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የማዳበሪያ ግዥ ሀሳቦችን በማቅረብ ሲፈቀድ ተግባራዊ እንዲሆን ደርጋል፣

16.8.3.3. ለተመረጡ አቅራቢ ድርጅቶች ስለሚገዛው ማዳበሪያ ዝርዝር መረጃ ወይም እስፔስፊኬሽን እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

16.8.3.4. የወቅቱን የዓለም የማዳበሪያ ዋጋ ከቴክኒክ ኮሚቴ የቀረበውን ሪፖርት ይገመግማል፣

16.8.3.5. ከመንግስት ሲፈቀድ ከተመረጡ አምራች ድርጅቶች ጋር በመደራደር በየዓመቱ በሚታደስ የረጅም ጊዜ የግዥ ኮንትራት መሠረት አሸናፊውን ይለያል፣ በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም ለሚኒስትር ዴኤታው ያቀርባል፣

16.8.4. የማዳበሪያ ግዥ የቴክኒክ ኮሚቴ

16.8.4.1. የማዳበሪያ ግዥ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፡-ኮሚቴዉ አባላት ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት ድርቶች የተውጣጣ እና የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክቶሬት | ሰብሳቢ |
| 2. | የግብርና ግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት | አባልና ፀሀፊ |
| 3. | የግብርና ትራንሰፎርሜሽን ኤጀንሲ | አባል |
| 4. | የብሄራዊ የአፈር ምርመራ ላብራቶሪ | አባል |
| 5. | የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት | አባል |

16.8.5. የማዳበሪያ ግዥ የቴክኒክ ኮሚቴዉ ተግባርና ኃላፊነት

16.8.5.1. የቀረበዉ የማዳበሪያ ፍላጎት በሀገሪቱ የአፈር ምርመራ ፍኖተ ካርታ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣል፤

16.8.5.2. ለምርት ዘመኑ የሚቀርበዉን የማዳበሪያ የጥራት ደረጃ መስፈርት እና የማዳበሪያ ዓይነት ይወስናል፣

16.8.5.3. ለሚገዛው ማዳበሪያ ዝርዝር መረጃ ወይም እስፔስፊኬሽን አዘጋጅቶ ወይንም በኢትዮጵያ ደረጃዎች የተዘጋጀውን በማረጋገጥ ለአብይ የማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ እና ለሚመለከታአዉ አካላት በጽሁፍ ያቀርባል፣

16.8.5.4. በተፈቀደው የግዥ ስርዓት የተመረጡት የማዳበሪያ አቅራቢ ድርጅቶች በተጠየቀዉ የማዳበሪያ አይነትና የጥራት ደረጃ ወይም ሰፐስፊኬሽን መሰረት የመወዳደሪያ ሰነድ ማቅረባቸዉን ያረጋግጣል፣ ለግብርና ግብዓት ግብይትና ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፡፡

## ክፍል አራ

## የማዳበሪያ አቅረቦት፣ የዋጋ አወሳሰን እና ስርጭት

17. የማዳበሪያ አቅርቦት

17.1. ክልሎች የክልላቸውን የማስረከቢያ ማዕከላት፣ ቦታ፣ የተረካቢ ስም፣ የማዳበሪያ ዓይነት፣ መጠን እና ቅድሚያ የሚሰጠውን ማዕከል በመለየት ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ያሳውቃል፤

17.2. አስመጪው በተሰጠው የግዥ ትዕዛዝ መሠረት የገዛውን ማዳበሪያ ከወደብ ወደ ማዕከላዊ መጋዘን በወቅቱ ያደርሳል፣

17.3. ክልሎች፣ ዩኒየኖች እና አሰራጮች በሀገር ውስጥ የሚመረተውን ማዳበሪያ ከአምራቾች በመግዛት ለሽያጭ ጣብያዎች ያቀርባሉ፤

17.4. አስመጪዎች ለግልና ለመንግስት እርሻዎች የሚያቀርቡትን ማዳበሪያ በፌዴራል የግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር እና የክልል ግብርናና እንስሳት ሀብት ቢሮች በሚሰጡት የድጋፍ ደብዳቤ መሠረት የሚያቀርቡ ይሆናል፣

17.5. ክልሎች ከማዕከላዊ መጋዘን አርሶ አደሩ ሊገዛ ወደሚችልበት የስርጭት ጣቢያዎች እንዲደርስ በየዞኑ የትራንስፖርት አገልግሎት ጨረታ አወጥቶ አሸነፊውን በመለየት በወቅቱ እንዲጓጓዝ ያደርጋል፡፡

18. የማዳበሪያ ዋጋ አወሳሰን

18.1. አስመጪው የማዳበሪያ ዋጋ እና የሀገር ውስጥ ወጪዎችን በማካተት ማዕከላዊ ማስረከቢያ ዋጋውን ለግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ያቀርባል፣

18.2. የግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴርም የክልል ግብርናና እንስሳት ሀብት ቢሮ ኃላፊ ወይም የቢሮ ኃላፊው ከሚወክለው ጋር በመሆን የቀረበው ዋጋ አስፈላጊ ዶክሜንቶችን በመርምር ይወስናሉ፣ለአስመጪዎች እና ለክልሎች ያሳውቃሉ፣

18.3. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወሰነውን ዋጋ መነሻ በማድረግ ከማዕከላዊ መጋዘን ክልሎች የአሰራጮችን ወጪ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እስከ ጣቢያ ያለውን ዋጋ የሚወስኑ ይሆናል፡፡

19. የማዳበሪያ ስርጭት

የማዳበሪያ ስርጭት ከውጭ የሚገባ ማዳበሪያን ከባህር ወደብ በቀጥታ ለአርሶ አደሩ የማቅረብ፣ ወይም ከውጭ ተገዝቶ የገባና ከባህር ወደብ ተጓጉዞ በተለያዩ ማዕከላዊ

የማከማቻና ማሰራጫ መጋዘኖች የተከማቸ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በዱቤ ወይም በካሽ ሽያጭ የማቅረብ ስራ ሂደት የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፤

19.1. አሰራጩ ከዞን የሥርጭት ጣቢያ የደረሰውን ማዳበሪያ የለምንም ማዘግየት እና የአርሶ አደሩ የዘር ወቅት (የመጠቀሚያ ወቅት) ከማለፉ በፊት ለተጠቃሚ አርሶ አደሮች እንዲደርስ ያደርጋል፣

19.2. አሰራጩ በዘመኑ ለየጣቢያው የቀረበውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለማዳበሪያ ክምችት የሚያገለግል ጥራቱን የጠበቀ መጋዘን በቅድሚያ ያዘጋጃል፣

19.3. አፈፃፀሙም በክልል የግብርና እና የእንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ የበላይነት ይመራል፡፡

## ክፍል አምስት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

20. የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር

20.1. የክልሎችን የፍላጎት ትንበያ አቅም በስልጠና በማጠናከር ሳይንሳዊ የትንበያ ስልቶች ስራ ላይ እንዲያውሉ በማድረግ ፍላጎት ትንበያ አሰራርን ያጎለብታል፣

20.2. ከውጭ ተገዝቶ መቅረብ ያለበት የማዳበሪያ አይነትና መጠን በመለየት የማዳበሪያ መግዣ የብድር ገንዘብ እና የውጭ ምንዛሬ እንዲመቻች ያደርጋል፣

20.3. ዓመታዊ የግዥ እና አቅርቦት የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች በወቅቱ ያሳውቃል፣ የማዳበሪያ ግዥ በወቅቱ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግዥ ህደቱንም በበላይነት ይመራል፣

20.4. ከየመርከቡ ለክልሎች እንዲሁም ለተረካቢ ማእከላት የሚደርሰውን የማዳበሪያ መጠን በዓይነት በመለየት መርከቦቹ የማራገፊያ ወደብ ከመድረሳቸው ከ10 ቀናት በፊት ለክልሎች በማሳወቅ በቂ መጋዘንና ተረካቢ ሠራተኞች በዩኒየኖች ወይም በተረካቢዎች በኩል እንዲዘጋጅ በማስደረግ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣

20.5. ማዳበሪያ በጊዜ ሠሌዳው መሰረት እየገባ መሆኑን በበላይነት ይከታተላል፣

20.6. በቂ መኪና እና የወደብ ማራገፊያ ቦታ ለማዳበሪያ እንዲመደብ ከትራንስፖርት ባለስልጣን እና ከማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን ጋር በቅርበት ይሰራል፣

20.7. ለክልሎች ወይም ዩኒየኖች ከየመርከቡ በየቀኑ መምጣት ያለበት መኪና መድረሱንና መራገፉን ከክልል ግብርና ቢሮዎች ወይም ተረካቢ ዩኒየኖች

መረጃ በመቀበል ማረጋገጥ፣ በማራገፍ ሂደት የገጠመ ችግር ካለ ከክልል ግብርና ቢሮዎች ወይም ህብረት ስራ ማስፋፊያ ኤጀንሲዎች ጋር በመነጋገር ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

20.8. እንደ አስፈላጊነቱ በየመረከቢያ ጣቢያዎች በመንቀሳቀስ በስልክ ከዩኒየኖች፣ አስራጮች እና ከክልሎች የሚደርሳቸውን መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣

20.9. በአጠቃላይ በማዳበሪያ አቅርቦቱና ስርጭት ላይ የዕለት ከዕለት ክትትል በማድረግ ማዳበሪያው በዕቅዱ መሰረት መቅረቡንና በወቅቱ ለአርሶ አደሩ መድረሱን ማረጋገጥ፣ ችግሮች በወቅቱ እልባት እንዲያገኙ ማድረግ እና ሌሎች ከዚህ ጋር የተገናኙ ስራዎችን በበላይነት ይመራል፡፡

21. የማዳበሪያው አስመጭ ድርጅት ተግባርና ሀላፊነት

21.1. በግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር የግብዓት ግብይት ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጀውን አጠቃላይ የምርት ዘመኑን የማዳበሪያ ግዥ መጠንና ዓይነት፣ የግዥ የጊዜ ሰሌዳ መረጃ ተከትሎ የማዳበሪያ ማስመጣት እቅድ ዝግጅት ያደርጋል፣

21.2. ዓለምአቀፍ የግዥ ጨረታ ወይንም ሲፈቀድ ሌላ አማራጭ የጊዥ ዘዴን በመጠቀም ዓለም አቀፍ አምራቾችን ወይም አቅራቢዎችን ለውድድር ይጋብዛል፣

21.3. የተወዳዳሪዎችን የመወዳደሪያ ሰነድ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ምዘና በማድረግ የግምገማ ውጤት ለግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ያቀርባል፣

21.4. የግምገማ ውጤቱን መሰረት አድርጎ የግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር አሸናፊውን ባሳወቀው በ15 ቀናት ዉስጥ አስመጭዉ ድርጅት ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የኮንትራት ውል ስምምነት ይፈርማል፣

21.5. ግዥው ዓለም አቀፍ ግዥ እንደመሆኑ መጠን ከአምራች ወይንም ከአስመጭ ጋር በተደረገው ውል ስምምነት መሰረት የመተማመኛ ሰነድ (Letter of Credit) በድርጅቱ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስከፍታል፣ ወይም ሌሎች አማራጮችን ይጠቀማል፡፡

21.6. ግዥ የተፈፀመበትን ማዳበሪያ ጭነው ወደብ የሚደርሱ መርከቦች አመጣጥ ይከታተላል፤ ይህንን መረጃ በየቀኑ ለግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር እንዲሁም ለክልሎች ያሳውቃል፤

21.7. ከወደብ ወደ ማዕከላዊ መጋዘን በተመጣጣኝ ዋጋ የማራገፊያ ማዕከላዊ መጋዘኖችን ከወደብ ያለውን ርቀት፣ እንዲሁም የተጫራቹን የማጓጓዝ አቅም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የትራንስፖርት አገልግሎት ጨረታ ያወጣል፣ ማዳበሪያው በቀጥታ ከመርከብ ወደ አጓጓዥ መኪኖች እንዲጫን ያደርጋል፣

21.8. በአሰራር ሂደቱ የተጠናከረ የክትትል እና የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት በየቀኑ ወቅታዊ መረጃዎችን ከሚመለከተው አካል ጋር ይለዋወጣል፣

21.9. ማዳበሪያው ወደተረካቢ ዩኒየኖች ከመጫኑ በፊት በየጣቢያው ባሉ የድርጅቱ ሰራተኞች አማካኝነት በክልሎች በኩል ክፍያ መፈጸሙና በመጋዘንና በተረካቢ ሰራተኞች ረገድ በቂ ዝግጅት መደረጉን በየጣቢያው በመንቀሳቀስ በአካል ያያል፣ ዝግጅት አለመደረጉ ከተረጋገጠም ለቀጣይ እርምጃ ይረዳ ዘንድ ከክልል ግብርና ቢሮዎች ወይም ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች ጋር በመመካከር ለጉዳዩ አፋጣኝ እልባት እንዲሰጥ ያደርጋል፣

21.10. ከእያንዳንዱ መርከብ በቀን ከሚራገፈው ማዳበሪያ ውስጥ ለእያንዳንዱ ተረካቢ መሄድ ያለበትን የመኪና ብዛትን በወደብ አካባቢ መኪና ለሚያሰማራው አካል ሰጥቶ በዕቅዱ መሰረት መኪኖች እየተሰማሩ መሆኑን ከትራንስፖርተሮች እና ከተረካቢ ዩኒየኖች መረጃ በማሰባሰብና በመከታተል ስምሪት አካባቢ ችግር ካለ በአፋጣኝ እንዲስተካከል ያደርጋል፣

21.11. መኪኖች ከወደብ ጭነው እንደተነሱ ለተረካቢ ክልሎች ግብርና ቢሮዎች ወይም ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች ያሳውቃል፣

21.12. በአንድ ማራገፊያ መጋዘን ከተጠቀሰው በላይ መኪና ተሰማርቶ ሳይራገፍ ከቆየ በትርፍነት ለሄዱት መኪኖች ዲመሬጅ ክፍያ ተጠያቂ ይሆናል፣

21.13. ከወደብ ለሚጓጓዘው ማዳበሪያ በቂ አስረካቢ ሠራተኞችን አስቀድሞ ያዘጋጃል፣ በራሱ ማዕከላዊ መጋዘን ለሚረከበው መጠን ማዳበሪያ በቂ መጋዘንና የሰው ሀይል ይመድባል፣

21.14. የኪሎ መጉደልና የባዕድ ነገር መደባለቅ ችግሮችን ለመቅረፍ የመጠንና ጥራት ተቆጣጣሪ ወክሎ በመመደብ ወደብ አካባቢ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ ያደርጋል፣

## 22. የክልል ግብርና ቢሮዎች እና ህብረት ስራ ኤጀንሲዎች

22.1. የክልሉን የማዳበሪያ ፍላጎት በማሰባሰብ፣ በማረጋገጥ እና በማጠናቀር ለፌደራል ግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ይልካል፤

22.2. ለማዳበሪያ መግዣ የሚውል የብድር ፍላጎት ይለያል፣ ለክልል ምክርቤት በማቅረብ ያፀድቃል፣ለሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ይልካል፡፡

22.3. በብድር የቀረበዉ ማዳበሪያ በቫውቸር ስርዓት ስራ ላይ እንዲዉልና ለብድር አመላለስ የክልሉ መንግስት ዋስትና እንዲገባ ያደርጋል፣

22.4. ከግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ከየመርከቡ የሚደርሰው ድልድል በተገለጸለት 3 ቀናት ውስጥ ከየመርከቦቹ ለየዩኒየኖቹ ወይም ማዕከላዊ መጋዘን የሚደርሰውን የማዳበሪያ መጠን በመለየት ለአስመጭው ድርጅትና ለተረካቢ ዩኒየኖች በማሳወቅ በቂ መጋዘንና ተረካቢ ሰራተኞች እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣

22.5. በተደለደላለቸው ማዳበሪያ መጠን ለሚከፈለው ገንዘብ ከአስመጪውና ከንግድ ባንክ ጋር ሶስትዮሽ ውል ይገባል፣

22.6. ጣቢያ ላይ ባሉት አስረካቢ ሠራተኞቹ አማካኝነት የየጣቢያውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በመከታተል ችግር ካለ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ መረጃ ይሰጣል፣ በየቀኑ በየጣቢያው የደረሰ መኪና፣ የተራገፈ መኪና፣ ያደረ መኪና፣ የገጠመ ችግር የሚገልጽ መረጃ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ይሰጣል፣

22.7. ከአስመጭው ድርጅት በሚደርሳቸው የክፍያ ጥያቄ መሰረት ተገቢውን ክፍያ በወቅቱ ይፈጽማሉ፤በወቅቱ ክፍያ ባለመፈፀማቸዉ ለሚደርሰው የባንክ ወለድና ሌሎች ወጭዎች ኪሳራ ለደረሰበት አካል ይከፍላሉ፣

22.8. ተረካቢዎች በቂ መጋዘኖችና ተረካቢ ሰራተኞች ማዘጋጀታቸውን በአካል ሄዶ በማረጋገጥ ለአስመጭው ድርጅትና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ያሳውቃል፣

22.9. ለእያንዳንዱ ዩኒየን በየቀኑ መቅረብ ያለበት የማዳበሪያ መጠን እየቀረበ መሆኑንና የቀረበው ማዳበሪያ ሙሉ በሙሉ እየተራገፈ መሆኑን በየቀኑ ከዩኒየኖችና ከአቅራቢው ድርጅት አረካካቢ ሰራተኞች መረጃ በመውሰድና በመከታተል መረጃውን በቀጣዩ ቀን ለእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስተር በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ያሳውቃሉ፣

22.10. በማራገፍ ሂደት ላይ ችግር የገጠመው ዩኒየን ካለ ችግሩን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣሉ፣

22.11. በዩኒየኖች አለመዘጋጀት ምክንያት ለሌላ ክልል ወይም ዩኒየን ተላልፎ በሚሰጠው ማዳበሪያ ምክንያት ለሚፈጠረው የአቅርቦት መጓተት ሀላፊነቱን ይወስዳሉ፣

22.12. ማዳበሪያዉ ከዩኒዬን ወደ መሰረታዊ ማህበራት፣ ከመሰረታዊ ማህበራት ለአርሶ አደር በፍላጎታቸው መሰረት መድረሱን ይከታተላሉ፣

22.13. በአጠቃላይ የሁኔታውን አሳሳቢነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አስፈላጊውን ሁሉ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማዳበሪያው በወቅቱ የሚገባበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ፣

22.14. ከወደብ ለተጓጓዘ ማዳበሪያ ሳይረገፍ በመዘግየት ለሚከሰተው ኪሳራ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

23. የትራንስፖርት ሚኒስቴር

23.1. በቋሚነት ለማዳበሪያ ማራገፊያ በቂ የሆነ የወደብ ማራገፊያ ቦታ እንዲፈቀድ ከወደብ አስተዳደር ጋር በመሆን ይሰራል፣

23.2. ወደብ አካባቢ የሚታየውን የመኪና ስምሪት እና የተዛባ የወደብ የማራገፊያ ቦታ አጠቃቀም ችግር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይፈታል፣

23.3. የወደብ ችግርን ለመቅረፍ አማራጭ ወደብ የማፈላለግና አዋጭ መሆኑን በማጥናት ለመንግስት አቅርቦ የማስወሰን ስራ ይሰራል፣

23.4. በየቀኑ ከጅቡቲ ወደብ ማዳበሪያ ጭነው የሚነሱ ተሸከርካሪዎች ብዛታቸውን፣ ወደ የትኛው ዩኒየን አሰራጭ ወይም እንደጫኑ፣ ማን አጓጓዥ እንደጫነ እና ለሎች መሰረታዊ የሎጂስቲክ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ሁሉ ፈጣን አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በየቀኑ ያስተላልፋል፣

23.5. የመኪና እንቅስቃሴው በትራንስፖርተሮች ፍቃድ ሳይሆን በስርጭት ፕሮግራሙ መሠረት እንዲሆን ያደርጋል፣

23.6. ለማዳበሪያ ማጓጓዣ አገልግሎት የሚውል በቂ ተሽከርካሪዎች ትራንስፖርተሮች እንዲያቀርቡ ከማዳበሪያ አስመጭው ድርጅት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

23.7. ማዳበሪያ ለማጓጓዝ ጨረታ አሸንፎ ግዴታውን በውሉ መሰረት በማይወጣ ትራንስፖርተር ላይ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የማዳበሪያ መጓጓዝ ስርዓቱ ሳይቋረጥ ወይም ሳይስተጓጎል እንዲቀጥል ያደርጋል፤

23.8. በአሰራር ሂደቱ ወቅታዊ መረጃዎችን ይለዋወጣል፣ ችግር ሲያጋጥም ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣል፣

23.9. የዲመሬጅ ሀጉ ተፈጻሚ እንዲሆን ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ይሰራል፣

23.10. አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ተባባሪ ትራንስፖርተሮች ወደ ማዳበሪያ ማጓጓዝ ሥራ እንዲገቡ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡

## 24. የኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት

24.1. ማዳበሪያው በተቀመጠው ስፔስፊኬሽን መሰረት ስለመሆኑ የላብራቶሪ ፍተሻና የኢንስፔክሽን አልግሎት በጥራትና በተቀመጠው ስታንደርድ መሠረት ለይቶ ያስረክባል፣

24.2. የአፈር ማዳበሪያው ከሚጫንበት ሀገር አስመጭው ድርጅት በወከላቸው የኢንስፔክሽን ኩባንያ የሚላከውን የምርቱን ወካይ ናሙናና የማሸጊያ ከረጢት ምርቱ ተጭኖ ከመንቀሳቀሱ በፊት ተረክቦ የላቦራቶሪ ፍተሻ በማድረግ ያለውን የጥራት ደረጃ በማረጋገጥ ለአስመጭው ሪፖርት ያቀርባል፣

24.3. የተጫነውን ምርት ማራገፊያ በባህር ወደብ ሲደርስ አስመጭው ድርጅት የወከላቸውን የኢንስፔክሽን ኩባንያ የድራፍት ሰርቬይ ሥራ በትክክል መስራታቸውን ያረጋግጣል፣

24.4. የባህር ወደብ የደረሰውን የምርት ናሙና በመውሰድ የፊዚካልና የኬሚካል ፍተሻ በማድረግ ለአስመጭው ድርጅት ሪፖርት ያቀርባል፣

24.5. የምርቱን ማሸጊያ ከረጢት መጠንና ጥራት ግምገማ በማድረግ ለአስመጭው ድርጅት ሪፖርት ያቀርባል፣

24.6. በባህር ወደብ ላይ የማራገፊያ ቦታንና የምርቱ ማሸጊያ ማሽኖችን ስራ ከመጀመራቸው በፊት ንጹህ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

24.7. የተመረጡት የኢንስፔክሽን ኩባንያዎች በማራገፊያ ባህር ወደብ ላይ ተገቢውን የድራፍት ሰርቬይ በማድረግ የሚዛኑን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ወይም የክብደትና የጭነት ቁጥጥር እያደረጉ ስለመሆናቸው ክትትል በማድረግ ሪፖርት ለአስመጭው ድርጅት በማቅረብ በሪፖርቱ ውስጥ የመጠን ልዩነት ካለ ወዲያውኑ ያሳውቃል፣

24.8. በአስመጭው ድርጅት የተመረጡት የትራንዚት አልገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተገቢውን የጭነት ቁጥጥር እያደረጉ ስለመሆናቸው ክትትል በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል፣

24.9. በአስመጭው ድርጅት የተመረጡት የትራንስፖርት ድርጅቶች የሚያቀርባቸው የጭነት መኪኖች ንጽህና ለምርቱ ጥራት መጓደል ምክንያት እንዳይሆን ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሪፖርት ያቀርባል፣

24.10. በማራገፍ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ወይም ሰርቪየር፣ ኢንስፔክሽን ኩባንያ፣ ትራንዚተርና የትራንስፖርት ድርጅቶች በማስተባበር ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው ክትትል በማድረግ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣

24.11. የማራገፍ ሥራ እንደተጠናቀቀ በማራገፍ ሥራ ላይ ተሳትፎ የነበራቸው ድርጅቶች የተራገፈውን የምርት መጠን በጋራ በማመሳከር ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ኢንስፔክሽን ኩባንያው በሚያዘጋጀው ሪፖርት ላይ አራቱም ኩባንያዎች ተስማምተዉ መፈረማቸውን ያረጋግጣል፣

24.12. የአንድ መርከብ የማራገፍ ሥራ እንደተጠናቀቀ ስለ አፈፃፀሙ ሪፖርት በማቅረብ በሪፖርቱ ላይ የሚመለከታቸው አካላት ውይይት እንዲያደርግባቸው ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ቅሬታ አቀራረብ

25. በማዳበሪያ አስመጭዎች እና በክልሎች ወይም በማዳበሪያ ሽያጭ ማዕከላት መካካል ቅሬታ በሚፈጠርበት ወቅት

25.1. ቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዳቸው በፊት ቅሬታውን ለመፍታት የሚያስችል የአፈታት ሂደት በውላቸው ውስጥ ያካትታሉ፤

25.2. በገቡት ውል መሰረት የማዳበሪያ ሽያጭ የሚያካሂዱ አካላት ቅሬታው በተነሳ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መፍታት ካልቻሉ ለሶስተኛ ወገን የሚመለከተው የወረዳ የግብርናና እንስሳት ሃብት ጽ/ቤት/ ያቀርባሉ፤

25.3. በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 20.2 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት ያልረካ ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ለህግ አካል ያቀርባል፡፡

26. አደርሶ አደሩ ወይም ከፊል አርብቶ አደሩ በማዳበያ ግብይት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱ ቅሬታ በሚኖረው ጊዜ ቅሬታውን ለሚመለከተው የወረዳ ግብርናና እንስሳት ሃብት ልማት ጽ/ቤትማቅረብ ይችላል፡፡

27. በአንቀጽ 2፶ በቀረበው ቅሬታ መሰረት

27.1. አርሶ አደሩ ቅሬታ ያቀረበበት የሽያጭ ማዕከል ህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ ቅሬታው በወረዳው በሕብረት ሥራ ማስፋፊያ ጽ/ቤት በሶስት ቀን ውስጥ ያቀርባል፣

27.2. አርሶአደሩ ቅሬታ ያቀረበበት የሽያጭ ማዕከል ግለሰብ ከሆነ ቅሬታው በወረዳ ግብርናና እንስሳት ሃብት ልማት ጽ/ቤት በሶስት ቀን ውስጥ ያቀርባል፡፡

28. አርሶ አደሮች በማዳበርያ ጥራት ጉድለት የተነሳ ቅሬታ በሚኖራቸው ጊዜ

28.1. በመጀመሪያ ደረጃ ቅሬታቸውን ለሽያጭ ወኪሉና ለወረዳ ግብርናና እንስሳት ሃብት ልማት ጽ/ቤት ወዲያውኑ ያቀርባሉ፡፡

28.2. በንዑስ አንቀጽ 27.1 በቀረበው ቅሬታ መሰረት ጽ/ቤቱ በራሱ ባለሙያዎች ቅሬታው በአምስት ቀን ውስጥ እንዲጣራ ያደረጋል፡፡

28.3. የጥራት ጉድለቱ መንስኤ በወረዳ ደረጃ የማይፈታ ከሆነ ጽ/ቤቱ የባለሙዎቹ ሪፖርት በደረሰው በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ የክልለ የየማዳበሪያ ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ያቀርባል፡፡

28.4. የክልል ማዳበሪያ ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሪፖርቱ ከወረዳ እንደቀረበለት አጣሪ የባለሙያዎች ቡድን ከአስመጪው ወይም አምራቹ ጋር በማቀናጀት በሁለት ቀናት ውስጥ ቅሬታ ወደቀረበበት ወረዳ ይልካል፡፡

28.5. በን/አንቀጽ 23.4 መሰረት የተላከው ቡድን

28.5.1. ቅሬታው ያለ ማዳበሪያ ናሙና ፍተሻ ሊፈታ የሚችል ከሆነ በአምስት ቀናት ውስጥ ለቀረበው ቅሬት በወረዳ ደረጃ መፍትሄ ይሰጣል፣

28.5.2. ቅሬታው የላቦራቶሪ ፍተሻ የሚጠይቅ ከሆነ ላቦራቶሪዎች ናሙና ወስደው እንዲፈትሹ እና ከ5 እስከ 10 ባሉት ቀናት ውስጥ በቀረበው የአርሶ አደሮች ቅሬታ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ይደረጋል፣

28.5.3. አርሶአደሮች የተሰጠው ውሳኔ ካለረካቸው ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለ ልዩ ለዩ ድንጋጌዎች

29. የተሻረ መመሪያ

29.1. የካቲት 1998 ዓ.ም የወጣ"የማዳበሪያ ግዥ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ስርጭት አጠቃላይ መመሪያ" ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡

30. መመሪያውን ማሻሻልና መተግበር

30.1. ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

31. መመሪያው የሚፈፀምበት ጊዜ

30.1. ይህ መመሪያ ከፀደቀበት --------- ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ግብርና እና እንስሳት ሀብት ሚኒስትር